
# የኒዮሊበራሊዝምና የኢህአዴግ ግብግብ (በአብዱራህማን አህመዲን፤ የቀድሞ የፓርላማ አባል)



December 6, 2014 - ትንታኔ

(ይህ ጽሑፍ በኅብረ-ብዕር መጽሔት ቅጽ 01 ቁጥር 02 ሕዳር 2007 እትም ላይ ታትሟል፡፡ መጽሔቱን ያላገኙ እንዲያነቡትና ለመወያየም ይሆን ዘንድ በዚህ ዌብሳይት ላይ እንዲታተም ተልኳል)

(Click here if you want to read it in PDF)

*መግቢያ*

"ኒዮሊበራሊዝም" የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ በተመለከተ መጣጥፍ ለማዘጋጀት አስቤ የነበረው፤ ስለጽንሰ ሃሳቡ ምንነት፣ ታሪካዊ አመጣጥ፣ በዓለምም ሆነ በሀገራችን ላይ ስላለው አንደምታ እና የሀገራችን ፖለቲከኞች በጉዳዩ ላይ የሚያራምዱትን አቋም በተመለከተ ዳሰሳ ለማድረግ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጽሁፉን በማዘጋጅበት ወቅት እና ጽሁፉን ካዘጋጀሁ በኋላ ሁለት አጋጣሚዎች ተፈጠሩ፡፡

አንደኛው አጋጣሚ ለጽሁፉ ዝግጅት የሚረዳኝን መረጃ በማሰባሰብበት ጊዜ እና በጉዳዩ ዙሪያ እያነበብኩ በሄድኩ ቁጥር፤ አሁን ካለው የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አብረው ሊታዩ የሚገባቸው መሰረታዊ ሃሳቦችን ማግኘት መቻሌ ሲሆን፤ ሁለተኛው አጋጣሚ ደግሞ በኒዮሊበራሊዝም ዙሪያ ሁለት ክፍል ያለው ጽሁፍ አዘጋጅቼ ካጠናቀቅኩ በኋላ ለአንድ የቅርብ ወዳጄ የሆነ የታሪክ ምሁር አሳየሁት፡፡

ይኸው ወዳጄ ጽሁፉን ካነበበ በኋላ "የግንዛቤ ብዥታ ያለው በኒዮሊበራሊዝም ላይ ብቻ አደለም፡፡ 'ልማታዊ መንግስት' በሚለው ጽንሰ ሃሳብም ዙሪያ የጠራ ግንዛቤ ያለ አይመስለኝም፡፡ በነካ እጅህ ይህንንም በተመለከተ ጻፍና በመጨረሻ በሁለቱ ጽንሰ ሃሳቦች ዙሪያ ያለውን ልዩነትና አንድነት እንዲሁም ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በየትኛው መንገድ ቢኬድ ያዋጣል የሚለውን መነሻ ሃሳብ ጨምረህ ብታቀርብ ይሻላል" የሚል አስተያየት ሰጠኝ፡፡

እውነቱን ለመናገር ኒዮሊበራሊዝምም ሆነ ገዢው ፓርቲ እከተለዋለሁ የሚለው የልማታዊ መንግስት (Developmental State theory) ንድፈ ሃሳቦች ተራ ነገሮች አደሉም፡፡ እንደ ኢትዮጵያዊም እንደ ዓለም ማህበረሰብ አካልም ሁላችንንም የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ህልውናችንን የሚነኩ ናቸው፡፡ በመሆኑም፤ በአንድ በኩል ያገኟቸውን መረጃዎች በተበጣጠሰ መልኩ ከማቅርባቸው ጊዜ ሰጥቼና ሰፋ አድርጌ በጽሁፌ አካትቼ ባቀርባቸው የተሻለ መሆኑን አመንኩ፣ በሌላ በኩል የወዳጄንም የተቀደሰ ሃሳብ ያለምንም ማንገራገር ተቀበልኩ፡፡

ከነዚህ ሁለት አጋጣሚዎች በተጨማሪ፤ በእውቀትና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ርእዮተ-ዓለማዊ ትንተና የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች በ 1960 ዎቹ ያደርጉት የነበረና ዛሬም በዚያው መንገድ ብንሄድ በየጓዳው ከምናሰማው ሮሮ፣ ሀሜትና አሉባልታ እንደሚያወጣንና ወደ ሰለጠነው አቅጣጫ እንደሚመራን በማሰብ፤ በጉዳዩ ላይ ከእኔ የተሻለ ግንዛቤና የትንተና ብቃት ያላቸው በተለያየ የሙያ መስክ (በፖለቲካ ሳይንስ፣ ሶሲዮሎጂ፣ ጂኦግራፊ፣ ኢኮኖሚክስ፣ ሕግ፣…) የተሰማሩ ሊቃውንት ተከታታይ ምሁራዊ ስራዎችን እንዲያቀርቡ ለመገፋፋት የሚረዳ የመነሻ ሃሳብ ማቅረብን መረጥኩ፡፡ በመጽሔቱ ዝግጅት ክፍልም በኩል ይኸው ሃሳብ ቅቡልነትን በማግኘቱ የጽሁፌን ይዘት እንደ ገና ፈተሸኩና ጽሁፉን ለጊዜው በሦስት ክፍል አዘጋጀሁት፡፡

በዚህ እትም ይገፔው የቀረብኩት የመጀመሪያው ክፍል በኒዮሊበራሊዝም ጽንሰ ሃሳባዊ ምንነት፣ ታሪካዊ አመጣጥና በዓለም ላይ በታየው አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ሁኔታዎች ዙሪያ የሚያተኩር ሲሆን፤ ሁለተኛው ክፍል በልማታዊ መንግስት ንድፈ ሃሳብ ምንነት፣ ታሪካዊ አመጣጥና በዓለም ላይ በታየው አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ሁኔታዎች ዙሪያ አጠር ያለ ዳሰሳ ለማቅረብ ይሞከራል፡፡ በመጨረሻም፤ የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ከሁለቱ ንድፈ ሃሳቦ አንጻር ለመዳደስ ይሞከራል፡፡

በተለይም ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ኒዮሊበራሊዝምን እንዲያ አገር ለማጥፋት ያደፈጠ ጭራቅ ቅድርጎ የሚያቀርበው እውነት ኒዮሊበራሊዝም ያን ያህል የገዘፈ አጥፊ ኃይል ስለሆነ ነው? ወይስ እኛን ያልገባን ኢህአዴግን ግን ልቡሰ-ጥላው (sub consciousness) የገረው ነገር ይኖር ይሆን? ወይስ ነገሩ ተራ የፖለቲካ ጨዋታ ነው?… ለመሆኑ ኢህአዴግ በተቀዋሚዎች ላይ ድምጹን ከፍ አድርጎ እንዲያ የሚጮኸው እውነት ኒዮሊበራሊዝም ለሀገራችን ስጋት ስለሆነ ነው? ወይስ ኒዮሊበራሊዝም በቅጡ ገብቷቸው ከልባቸው አምነው የተቀበሉ "ፖለቲከኞች" በሀገራችን አሉ ብሎ ነው? ወይስ ለማደናገር? ለመሆኑ ራሱ ኢህአዴግ የኒዮሊበራሊዝምን ተጽእኖ በአግባቡ ተከላክሏልና ነው ተቃዋሚዎች ላይ ጣቱን የሚቀስረው?… ኧረ! ለመሆኑ ኢህአዴግ የከበርቴ ሀገሮችን (ሲፈልግ የልማት አጋሮቼ ይላቸዋል) እርዳታ፣ ብድርና ድጋፍ እንክት አድርጎ እየተጠቀመ መለስ ብሎ ጭራቅነታውን ጮክ ብሎ የሚነግረን አማርኛ አይሰሙም ብሎ ነው ወይስ አሁንም እኛን ለማደናገር?

ይህንንም እንተወውና… ከአልባኒያ ሶሻሊዝም እስከ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የተለያዩ የርዕዮተ ዓለም ንድፈ ሃሳቦችን እያነሳ በመጣል የሚታወቀው ኢህአዴግ (ይህንን የኢህአዴግ አካሄድ የፖለቲካ ሰለሜ እለዋለሁ እኔ) አሁን አሁን እከተለዋለሁ እያለ በስፋት የሚደሰኩርለት የ"ልማታዊ መንግስት" ንድፈ ሃሳብስ ቢሆን እውነት ኢህአዴግ እንደሚለው ሕዝብን ተጠቃሚ፣ ሀገርን የበርሃ ገነት የሚያደርግ ልማት ያመጣል? ወይስ እንደ ውሃ ማቆር፣ ውጤት ተኮር፣….

ወዘተ. አንድ ሰሞን ያዙኝ ልቀቁኝ ካለ በኋላ ሌላ “ፕሮግረሲቭ” ምናምን የሚል ነገር በማምጣት የተለመደ የፖለቲካ ሰለሜውን ሊያሳየን?… ኸረ! ለመሆኑ የልማታዊ መንግስት መጨረሻ ግቡ ምንድነው? ግለሰብ ካፒታሊስቶችን መፍጠር? ወይስ ትንሽ ቆየት ብሎ “ልማታዊ ካፒታሊስቶች” ሊለን ይሆን?… ወይስ ግለሰብ ከበርቴዎችን ሳይሆን ከበርቴ መንግስትን ለመፍጠር (to create state capitalism) የታለመ አቅጣጫ ነው እንባል ይሆን?… የሚሉትን ሃሳቦች በማንሳት ዳሰሳ ለማድረግ ይሞከራል፡፡ (አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቃላትን ቃል በቃል ልተረጉማቸው ባለመቻሌ ወይም ብተረጉማቸውም ጽንሰ ሃሳቡን በጥሩ ሁኔታ ይገልጹታል ብዬ ስላላሰብኩ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አልፎ አልፎ የእንግሊዝኛውን ቃል እንዳለ ተጠቅሜአለሁ፡፡ ለዚህም ከፍ ያለ ይቅርታ እጠይቃለሁ)

ጽንሰ ሃሳቡ

በአንድ ጉዳይ ላይ ለመግባባት ወይም ላለመግባባት ከተፈለገ በቅድሚያ በጉዳዩ ምንነትና ባህሪያት ዙሪያ ስምምነት የተደረሰበት ትርጉም (ማብራሪያ) ማስቀመጥና የጋራ ግንዛቤ መፍጠር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ አንዳንድ ቃላት ወይም ጽንሰ ሃሳቦች ማንኛውም ሰው በቀላሉ የሚረዳቸው በመሆኑ በእንደዚያ ዓይነት ጉዳዮች ላይ ብዙ ውጣ ውረድ ሳይኖር መግባባት ይቻላል፡፡ አንዳንዶቹ ግን ከአመጣጣቸው ጀምሮ በውስብስብ ሁኔታዎች ውስጥ የሚያልፉ፣ ውስብስብ ነገሮችን የሚገልጹ፣ የተለየ ቴክኒካዊ ሙያና እውቀት (ፕሮፌሽን) የሚጠይቁ በመሆኑ ሁሉም ሰው በእኩል ደረጃ፣ ጥርት ባለ ሁኔታ፣ ያለምንም ብዥታ ሊረዳቸውም ሆነ ሊገነዘባቸው አይችልም፡፡ እናም በእንደነዚህ ዓይነት ሃሳቦች ላይ ሁሉም ሰው ስሜቱን፣ ምኞቱንና ፍላጎቱን የሚያንጸባርቅ ትርጉም እየሰጠ ልዩነቶችን ከሚያሰፋ ለጉዳዩ ቅርብ የሆኑ ሰዎች የሰጧቸውን ብያኔዎች በተናጠል በማየት የጋራ የሆኑ ትርጉሞችን መፈለግ ብልህነት ይመስለኛል፡፡ ከያዝነው ርእሰ ጉዳይ አኳያ፤ “ኒዮሊበራሊዝም” የሚለውን ቃል ብቻውን አቁመን ብንተረጉመው “አዲሱ ሊበራሊዝም” ከማለት ውጪ ሰፊ ግንዛቤ የሚሰጥ ትርጉም ልናገኝለት አንችልም፡፡ በመሆኑም፤ በጽንሰ ሃሳቡ ምንነትና ትርጉም ዙሪያ የተለያዩ ሰዎች የሰጡትን ትርጉምና ብያኔ ማየቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ኒዮሊበራሊዝም የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በዓለም የኢኮኖሚ መድረክ ላይ መገለጽ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በምሁራንና በፖለቲከኞች መካከል ለአርባ ዓመታት ያህል አጨቃጫቂ ሆኖ እንደቀጠለ ነው፡፡ በዚህም ባህሪው ምክንያት አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም ሊበጅለት አልቻለም፡፡ ይሁን እንጂ ኒዮሊበራሊዝምን ከአራት አቅጣጫዎች ማየት እንደሚቻል በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ይኸውም፡- ኒዮሊበራሊዝም ከኢኮኖሚ ንድፈ ሃሳብ (ቲዎሪ) አኳያ፣ ኒዮሊበራሊዝም ከርዕዮተ ዓለም አኳያ፣ ኒዮሊበራሊዝም ከፖሊሲ ሞዴልነት (Paradigm) አኳያ እና ኒዮሊበራሊዝም ከማህበራዊ ጉዳይ አኳያ በማለት ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

“የክላሲካል ሊበራሊዝም አስተሳሰብ የመንግስት ሚና ከዘበኛነት አይለፍ፡፡ የፍትህና የፀጥታ ተቋማትን ብቻ እንዲመራ ይደረግ፡፡ የንግድ ልውውጡ በዜጎች ይከናወን… የሚል መንፈስ አለው፡፡ በዚህም ምክንያት በክላሲካል ሊበራሊዝም እና በኒዮሊበራሊዝም መካከል ያን ያህል የተራራቀ ልዩነት አለ ለማለት አያስደፍርም” ይላሉ በኦስሎ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሣይንስ መካነ ትምህርት መምህር የሆኑት ዳግ ኤር ቶርሰን እና አሙንድ ሌይ፡፡

ከክላሲካል ሊበራሊዝም በኋላ የታየው “ሞደርን ሊበራሊዝም” ግን መንግስት በኢኮኖሚው ላይ ሚና እንዲኖረው ይፈቅዳል፡፡ ይህም የመንግስት ሚና የገበያ ቦታዎችን ማመቻቸት እና ለብዙሃኑ ህብረተሰብ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃና አገልግሎቶችን ማቅረብን ይጨምራል፡፡ እንዲህ ያለው ሞደርን ሊበራል አስተሳሰብ ከ 19 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቴዎሪስቶች ቤንጃሚን ኮንስታንት እና ጆን ስቱዋርት ሚልን ይጨምራል፡፡ በቅርብ ዓመታትም ጆን ደዌ፣ ዊሊያም ቢቨሪጅ እና ጆን ራውልስም ተመሳሳይ ሃሳብ ማራመዳቸው ይነገራል፡፡

ዴቪድ ሀርቬይ የተባለ የጂኦግራፊ ምሁር በበኩሉ ሊበራሊዝምን በሚያራምዱ ወገኖች መካከል ያለውን ልዩነት አመልክቷል፡፡ “ኒዮሊበራሊዝም ለግለሰብ መብትና ለግል ሀብት ባለቤትነት መብት ትኩረት የሚሰጥ የፖለቲካ ፍልስፍና ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ወጥ ፍልስፍና አደለም፡፡ በድምዳሜዎቹም ይሁን በመርሆዎቹ ዙሪያ ሰፊ ልዩነቶች ይንጸባረቃሉ፡፡ በአንድ በኩል መንግስት አይኑር የሚል የለየለት መንግስትን የሚያፈርስ ‘ልቅነትን’ (laissez-faire) ይሰብካል፤ ይህም ‘አናርኮ-ሊበራሊዝም’ (anarcho-liberalism) ያሰኘዋል፡፡ በሌላ በኩል፣ መንግስት ዘበኛ ይሁን የሚል የክላሲካል ሊበራሊዝምን አመለካከት ያራምዳል” ይላሉ ሀርቬይ፡፡ በዚህም ምክንያት በሊበራሊስቶች መካከል ያለው የጋራ ዓላማ፣ እምነትም ሆነ አስተሳሰብ ምን እንደሆነ ግልጽ አድርጎ ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው፡፡

ኒዮሊበራሊዝምን ከኢኮኖሚ ንድፈ ሃሳብ አኳያ የሚያዩት ደግሞ፤ “ኒዮሊበራሊዝም የዋጋ ቁጥጥርን ለማጥፋት፣ የካፒታል ገበያን ለመፍጠር፣ የንግድ መሰናክሎችን ለማስወገድ፣ የመንግስትን ጣልቃ ገብነት ለማስቀረት፣… የሚወሰድ የኢኮኖሚ መርህ” እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ኒዮሊበራሊዝምን “እንደ እድገት ሞዴል – መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ስርዓትን ለማስወገድ፤ እንደ አይዲዮሎጂ – የሰውን ልጅ ነፃነት ለማረጋገጥና የመንግስትን ጉልበት ለማሳነስ” የመጣ አድርገው ያቀርቡታል፡፡

እ.ኤ.አ ከ 1960 ዎቹ እና 1970 ዎቹ በኋላ እየተቀነቀነ ያለው የኒዮሊበራሊዝም አስተሳሰብ ግን፣ መንግስትን አሳንሰው የዘበኛነት ሚና ይኑረው ከሚሉት ከቀዳሚዎቹ (ክላሲካል) ሊበራሊዝም የተለየ መሆኑን በርካታ ሰነዶች ያስረዳሉ፡፡ ለምሣሌ፡- ጀርመናዊው ምሁር አሌክሳንደር ሩስቶው ሊበራሊዝምን “ለዋጋ ቅድሚያ የሚሰጥ፣ ነፃ የኢንተርፕራይዝ የውድድር ስርዓት ያለው፣ ጠንካራና ገለልተኛ የመንግስት ስርዓት ያለው…” በማለት ይተረጉመዋል፡፡ “የመንግስት ጣልቃ ገብነትን የሚፈቅድ ዘመናዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲ” ነውም ይለዋል ሩስቶው፡፡

ከፖለቲካ ንድፈ ሃሳብ አንጻር የሚመለከቱት ደግሞ፤ “ኒዮሊበራሊዝም የሚለው ጽንሰ ሃሳብ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ፍልስፍናን ያመለክታል” ይላሉ፡፡

አያይዘውም፣ የኒዮሊበራሊዝም ፍልስፍና በአንድ ሀገር ኢኮኖሚ መንግስት ያለውን የጣልቃ ገብነት ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን፤ ከዓለም አቀፍ ግንኙነት አኳያ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ መርህን ተከትሎ ዓለም አቀፍ ንግድ እንዲስፋፋ፣ ሀገሮች ድንበራቸውን ለሸቀጦችና አገልግሎቶች ዝውውር ክፍት እንዲያደርጉ… የሚል መርህ ያስቀምጣል ይላሉ፡፡

ሌሎች ወገኖች በበኩላቸው “ኒዮሊበራሊዝም የኢኮኖሚ ርዕዮተ-ዓለም (economic ideology) ነው” ይላሉ፡፡ የእነዚህ ወገኖች ማዕከላዊ ነጥብ “ነፃ ገበያ፣ ነፃ የንግድ ስርዓት፣ ያልተገደበ የካፒታል ፍሰት እና ድንበር የለሽ የንግድ ግንኙነት (ግሎባላይዜሽን) መኖር አለበት” የሚል ነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ተግባራዊ ሲደረጉ ከፍ ያለ የኢኮኖሚ እድገት ይገኛል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የመንግስትን ወጪ መቀነስ፣ በወጪ ንግድ ላይ ግብርና ታክስን መቀነስ፣ ዓለም አቀፍ ንግድን የሚያሰናክሉ ህጎችን ማስወገድ፣ የመንግስትና የህዝብ ተቋማትን ወደ ግል ይዞታ ማዞር፣ የመንግስትን ጣልቃ ገብነት ማስወገድ፣… አስፈላጊ መሆኑን የኒዮሊበራሊዝም ርዕዮት አቀንቃኞች ያስተምራሉ፡፡

“ኒዮሊበራሊዝም ዓለም አቀፍ ሜጋ ኩባንያዎች በየትኛውም የዓለም ክፍል መዋዕለ ንዋያቸውን አፍስሰው ሀብት እንዲያፈሩና ትርፍ እንዲያካብቱ መንገዱ ሁሉ ክፍት ይሁንላቸው፣ በሀገሮች ድንበር ላይ ያሉ ኬላዎች ይነሱላቸው፣ የመንግስት ቢሮክራሲ ይወገድላቸው፣ ታክስና ቀረጥ ይቀነስላቸው፣ መንግስት ሰላምና ደህንነታቸውን የሚጠብቅ ዘበኛ ሆኖ ያገልግላቸው እንጂ ንግድ ከሚባል ነገር ውስጥ እጁን አይዱል፣… ማለት ነው” የሚሉም አሉ፡፡

ኒዮሊበራሊዝም ማለት፤ “የከበርቴዎች ኢንዱስትሪዎች የበከሉት አካባቢ ጥበቃ ይደረግለት ሲባል አይመለከተኝም የሚል፣ በሀገሮች መካከል ታሪፍና ፍትሃዊ የንግድ ግንኙነት እንዲኖር የማይሻ፣ ሶሻሊዝምን የሚነቅፍ፣ ሁሉም ጉልበቱን ሸጦ ያግኝ እንጂ ማህበራዊ ዋስትና ይደረግ የማይል፣ ህብረተሰቡ ለሚጠቀምባቸው መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎች ድጎማ እንዲደረግ የማይፈልግ፣ ከበርቴዎች ኪሳራ ሲደርስባቸው ግን የማካካሻ ድጎማ (Bailout) ይደረግ የሚል፣ የታዳጊ ሀገር መንግስታት ምንም ዓይነት የታሪፍ ከለላ ወይም ድጎማ እንዲያደርጉ የማይሻ፣ የከበርቴ ሀገራት መንግስታት የታሪፍ ከለላና ለገበሬዎቻቸው ድጎማ ሲያደርጉ ግን ተቃውሞ የማያሰማ፣…. ነው” የሚሉም ወገኖች አሉ፡፡ “The Socialist” የተሰኘው መጽሔት ተባባሪ አዘጋጅ የሆነው አሜሪካዊው ምሁር ሮበርት ማክቼንሲ በበኩሉ፤ “ኒዮሊበራሊዝም ማለት ጓንቱን ያወለቀ ካፒታሊዝም ነው” ይለዋል፡፡

በአጠቃላይ፤ ከበርካታ የኒዮሊበራሊዝም ትርጓሜዎችና ትንታኔዎች ላይ ማስተዋል የሚቻለው ኒዮሊበራሊዝም ስንል ኢኮኖሚያዊ ሊብራላይዜሽን፣ ፕራይቬታይዜሽን፣ ነፃ ገበያ፣ ነፃ ንግድ፣ ዲሬጉሌሽን፣ የመንግስት ወጪ ቅነሳ፣ የታሪፍ ከለላ፣ የመንግስት ጣልቃ ገብነት አለመኖር፣… ወዘተ. ጋር የተያያዙ የኢኮኖሚ መርሆዎችን ያጠቃልላል፡፡ እንግዲህ እነዚህ ከላይ የተጠቃቀሱት ሁሉ ተደማምረው ነው የኒዮሊበራሊዝምን ትርጉምና ምንነት የሚገልጹልን፡፡

ታሪካዊ አመጣጡ

“Neo” (ኒዮ) የሚለው ቃል፤ “New” (አዲስ) ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የተገኘ ነው፡፡ “ኒዮሊበራሊዝም” የሚለውን ሃሳብ ቃል በቃል ስንተረጉመው “አዲሱ ሊበራሊዝም” ማለት ይሆናል፡፡ “አዲሱ ሊበራሊዝም” ስንል ደግሞ፤ “አሮጌ፣ ጊዜ ያለፈበት፣ ፋሽንነቱ ያለቀበት፣…” ሌላ የሊበራሊዝም ዓይነት እንደነበረ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም፤ ስለአዲሱ ለማወቅ የአሮጌውን ምንነት ወደኋላ መለስ ብሎ መቃኘቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

“ሊበራሊዝም” የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ በተብራራ መልኩ የቀረበው ታዋቂው የስኮቲሽ ኢኮኖሚስት አዳም ስሚዝ ‘የሀገሮች ሀብት’ (Wealth of Nations) በሚል ርእስ እ.ኤ.አ በ 1776 ባሳተመው መጽሐፍ ውስጥ መሆኑ ይነገራል፡፡ አዳም ስሚዝ በዚህ መጽሐፉ ላይ በዋናነት ትኩረት አድርጎ ያቀረበው “መንግስት በኢኮኖሚ ጉዳይ ጣልቃ መግባት የለበትም፡፡… በማኑፋክቸሪንግ ላይ ገደብ መኖር የለበትም…. በንግድ ልውውጥ ላይ መሰናክል መኖር የለበትም… ታሪፍ መኖር የለበትም…. ነፃ ገበያ ለሀገሮች እድገት አስፈላጊ ነው….” የሚሉትን ከዚያ በፊት በነበሩ የኢኮኖሚ መርሆዎች ላይ ያልተንጸባረቁ ሃሳቦች ነበር፡፡

ይህም የአዳም ስሚዝ ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ “የለበትም፣ የለበትም…” በሚሉ ቃላት ታጅቦ የቀረበ በመሆኑ “ሊበራል” (ነፃ) የሚል ትርጉም ተሰጠው፡፡ ይህም ትርጉም እየሰፋ በመሄድ “ነፃ ገበያ፣ ነፃ ውድድር፣…” የሚሉትንና መሰል ለከበርቴዎች ትርፍ መካበት የሚረዱ ሃሳቦችን እየጨማመረና ከግለሰብ መብቶችና ነፃነቶች ጋር እየተቆራኘ እ.ኤ.አ እስከ 1930 ዎቹ የኢኮኖሚ ውድቀት ድረስ እንደዘለቀ ጥቂት የማይሰኙ አእሩግ ሰነዶች ያመለክታሉ፡፡

እ.ኤ.አ በ 1930 ዎቹ በዓለም ላይ የታየው ታላቁ የኢኮኖሚ ውድቀት ሲከሰት እንደ ጆን ሜይናርድ ኬነስ ያሉ የኢኮኖሚ ሊቆች፣ የመንግስትን ጣልቃ ገብነት የሚቃወመውን የአዳም ስሚዝን “ሊበራል” አስተሳሰብ በመተቸት አዳዲስ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አቅጣጫዎችን የሚያመላክቱ ንድፈ ሃሳቦችን ያፈልቁ ጀመር፡፡ “ባለሀብቶች የበለጠ ሀብት ለማካበት የሚጠቅማቸው ነፃ ገበያ ሳይሆን የመንግስት ጣልቃገብነት ነው…” የሚለውን አስተሳሰብ የሚያራምዱት ጆን ሜይናርድ ኬነስ እና በዙሪያው የነበሩ ኢኮኖሚስቶችም “ኬነስያን” (Keynesian) የሚል ጥቅል መጠሪያን ያገኙት የአዳም ስሚዝን ሊበራል አስተሳሰብ በመተቸት ባቀረቡት አማራጭ መሆኑ ይነገራል፡፡

የኬነስያን አስተሳሰብ እ.ኤ.አ ከ 1930 ዎቹ ጀምሮ በአውሮጳ ሀገሮች ስራ ላይ ውሎ የኢኮኖሚ መረጋጋት እየፈጠረና እየገነነ በመጣበት ወቅት ሊበራሊዝም ሙሉ ለሙሉ ወደ ታሪክ መዘክር ባይወረወርም ወረቱ አልቆበት “embedded liberalism” (ትክል ሊበራሊዝም) በሚል ተተክቶ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል፡፡

የኬነስያን የኢኮኖሚ ፖሊሲ አቅጣጫ እ.ኤ.አ እስከ 1950 ዎቹ እና 1960 ዎቹ ድረስ መልካም የኢኮኖሚ መረጋጋትና እድገት ማምጣት አስችሏል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህ የኢኮኖሚ ሞዴል ከፍተኛ ምርታማነት እንዲፈጠር ቢያደርግም ኢኮኖሚውን ከዚያ በላይ ይዞት ሊሄድ ባለመቻሉ፤ በ 1970 ዎቹ መጀመሪያ

አካባቢ በዓለም ላይ ከፍተኛ የሸቀጦች ዋጋ ማጣት (የምርት መትረፍረፍ)፣ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝና ግሽበት ተከሰተ፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት መፍትሄ በሚፈለግበት ወቅት ሊበራሊዝም አንዱ አማራጭ ሆኖ ቀረበ፡፡ በዚህ ወቅት የተነሳው ሊበራል አስተሳሰብ ከቀዳሚው (ክላሲካል ሊበራሊዝም) ጋር ልዩነት ያለው መሆኑን ለማመልከትም "New Liberalism" (NeoLiberalism) የሚል ስያሜ ተሰጠው፡፡

ኒዮሊበራሊዝም ግልጽ ባለ ሁኔታ ይፋ ሆነ የሚባለው ግን እ.ኤ.አ በ 1950 ዎቹ አጋማሽ ላይ ስለ ኒዮሊበራሊዝም የሚያትት መጽሐፍ በጀርመን ሀገር ከታተመ በኋላ መሆኑን አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ኒዮሊበራሊዝም እንደ ርዕዮተ-ዓለማዊ እንቅስቃሴ ሮበርት ሞንዴል እና አርተር ፍሌሚንግ በተባሉ ምሁራን ስራዎች ውስጥ በስፋት የተንጸባረቀ ሲሆን፤ በዚሁ ጊዜ ፍሬድሪክ ሄይክ፣ ሚልተን ፍሬድማን እና ሚካኤል ፖላይኒ የተሰኙ ምሁራን በእንግሊዝ ሀገር የነፃ ገበያን መርህ የሚያቀነቅን ድጋፍና ምክር ሰጪ አካል (think tank) በማቋቋም እ.ኤ.አ በ 1960 ዎቹ እና 1970 ዎቹ የኒዮሊበራሊዝም እንቅስቃሴ ያደርጉ እንደነበርም ሌሎች መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

የኒዮሊበራሊዝም አስተሳሰብ ከምእራባውያን የፖሊሲ አቅጣጫነት ወጣ ብሎ በዓለም መድረክ ላይ መታየት የጀመረው ግን እ.ኤ.አ. በ 1973 መሆኑ ይነገራል፡፡ በዚያ ወቅት የነዳጅ ላኪ (ኦፔክ) ሀገሮች ማዕቀብ ሲጥሉ አሜሪካ በበኩሏ ይህን ያደረጉ የዓረብ ሀገራት ከነዳጅ ሽያጭ ያገኙትን ተቀማጭ ገንዘብ (ፔትሮ ዶላር) በአሜሪካ ባንኮች እንዲቀመጥ ካላደረጉ ጦርነት እከፍታለሁ አለች፡፡ ጦርነትን የፈሩት ዓረቦችም የተጠየቁትን በማድረግ ከአሜሪካ የተሰነዘረባቸውን ዛቻ አበረዱ፡፡

የአሜሪካ ባንኮች በአጋጣሚ ካዝናቸው የገባውን ገንዘብ ኢኮኖሚው መነቃነቅ አቅቶት በተቸከለበት ሁኔታ ምን እንደሚያደርጉት ጨነቃቸው፡፡ በመጨረሻም ለድሃ ታዳጊ ሀገሮች ከፍ ባለ ወለድ በማበደር ትርፍ ማጋበስ እንደሚቻል አሰቡ፡፡ የባንኮቹ እሳቤ ይህንን ገንዘብ የሚበደሩት ግለሰቦች ሳይሆኑ መንግስታት ስለሆኑ ብድሩን በኃላፊነት መንፈስ ይመልሳሉ፣ ምንም ዓይነት ኪሳራም አይመጣም የሚል ግምት እንደነበራቸው ይነገራል፡፡

ይሁን እንጂ፤ የወለዱ መጠን ድሃ ሀገሮች ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ በማሻቀቡ ከላቲን አሜሪካዋ ሜክሲኮ ጀምሮ በርካታ የ 3 ኛው ዓለም ሀገሮች በዕዳ ጫና ናላቸው ተበጠበጠ፡፡ የብድር ቀውስ ተፈጠረ፡፡ የአሜሪካ ባንኮችም ችግር ላይ ወደቁ፡፡ አሜሪካ ይህንን ብድር ለማስመለስ ዘዴ ቀየሰች፡፡ ይኸውም፤ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ለ 3 ኛው ዓለም ሀገሮች ለእዳ ክፍያ የሚሆን ብድር እንዲሰጣቸው በማድረግ ተበዳሪዎቹ እዳቸውን ከነወለዱ አስልተው ለአሜሪካ ባንኮች እንዲመልሱ ማድረግ ነው፡፡

ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት በበኩሉ ይህንን የብድር መመለሻ ብድር ለማበደር ቅድመ ሁኔታዎችን ዘርዝሮ አስቀመጠ፡፡ ከቅድመ ሁኔታዎቹ አንዱ ደግሞ የ 3 ኛው ዓለም ሀገራት ብድር ማግኘት ከፈለጉ የመዋቅር ማስተካከያ (structural adjustment) እንዲያደርጉ የሚያስገድድ ነው፡፡ ከመዋቅር ማስተካከያውም ጋር፤ በመንግስት ይዞታ ስር ያሉ ተቋማትን ሽጡ፣ የመንግስትን ድጎማ አስቀሩ፣ የታሪፍ ቅነሳ አድርጉ፣… የሚሉ ተጨማሪ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታዎች ተደረደሩ፡፡

እነዚህ ዋነኛ የኒዮሊበራል መርሆዎች በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ብድር ፈቃጅነት እና በዓለም ባንክ አበዳሪነት ተግባራዊ እንዲደረጉ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ማርጋሬት ታቸር እና በወቅቱ የአሜሪካን ፕሬዝዳንት የነበሩት ሮናልድ ሬገን በየሀገሮቻቸው ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ ባሉ ሀገሮች የመዋቅር ማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ አስፈላጊውን ግፊት አድርገዋል፣ በተግባርም ተፈጽሟል፡፡ ታቸር "ከግሎባል ካፒታሊዝም ውጪ አማራጭ የለም" ያሉትም በዚሁ ወቅት ነበር፡፡ በዚሁ መሰረትም፣ በርካታ ታዳጊ ሀገሮች ለድንበር ዘለል ኩባንያዎች በራቸውን እየበረገዱ እስከ ጓዳ ጎድጓዳቸው ድረስ ዘልቀው እንዲገቡ አድርገዋል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ የኒዮሊበራል አስተሳሰብ በተለይ የሦስተኛ ዓለም ሀገሮች መንግስታትን ያስደሰተ ባለመሆኑ አንዳንድ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ጭምር "ኒዮሊበራሊዝም የሞራል ዝቅጠት ያመጣል፡፡ ስለሆነም የገንዘብ ተቋማትና ያደጉ ሀገራት ለታዳጊ ሀገሮች የገንዘብ ድጋፍ (Bailout) ሊያደርጉ ይገባል" የሚል አስተያየት እስከመሰንዘር ደርሰው እንደነበርና ሂደትና ውጤቱም የገንዘብ መቅለጥን (currency melt down) እንዳስከተለ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት እና ዓለም ባንክ በዚህ መልኩ የታዳጊ ሀገሮችን ኢኮኖሚ ከ 1980 ዎቹ ጀምረው ሲያመሳቅሉት ከከረሙ በኋላ፤ ታዳጊ ሀገሮች በምዕራብ ሀገሮች ገበያ ላይ ምርታችሁን ለመሸጥ ይረዳችኋል በሚል ሰበብም General Agreement on Trade and Tariffs, North American Free Trade Agreement, European Union,… የመሳሰሉት አካባቢያዊ የንግድ ቀጣናዎች እንዲመሰረቱ፣ የዓለም የንግድ ድርጅት (WTO) አባል እንዲሆኑ፣ በእነዚህ ስምምነቶች መሰረት የታሪፍ ከለላ እንዲያነሱ፣… ወዘተ. ተደርገዋል፡፡

በ 1980 ዎቹ ወደ ስልጣን የመጡት ሮናልድ ሬጋን የወሰዱት እርምጃ ሀብት ያላቸው የአሜሪካ ከበርቴዎች ገንዘባቸውን አዋጭነት ባላቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ አፍስሰው የተዋጣለት ትርፍ እንዲያገኙ በማድረግና ከዚያ የሚገኘው ገቢ በተንጠባጠበ መልኩ ወደ ህብረተሰቡ እንዲገባ ማድረግ ነበር፡፡ ይህም በኢኮኖሚ ባለሙያዎች "Trickle down Effect" የሚባለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሀብታሞችን የበለጠ ሀብታም በሚያደርገው የሬገን ፖሊሲ ውስጥ የብዙሃን ድሃዎችን ሕይወት የሚለውጥ ሁኔታ ሊገኝ አልቻለም፡፡ የከበርቴዎቹ የበለጠ ሀብት ማካበትም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ አሳድጎ አሜሪካንን ከቁጥር አንድ ተበዳሪነቷ ሲያወጣት አልታየም፡፡

እነዚህ ሁኔታዎች እየተባባሱ በመምጣታቸውም እ.ኤ.አ በ 2008 ዓ.ም የተከሰተው የፋይናንስ ቀውስ ሊፈጠር እንደቻለ የሚታወቅ ሲሆን፤ ይህም ኒዮሊበራሊዝም ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ሚና ሊጫወት የማይችል፣ ይልቁንም የጥቂት ከበርቴ የፖለቲካ ልሒቃንን ስልጣን ለማጽናት የረዳ መንገድ ነው

ይላሉ ኢኮኖሚስቱ ጃሶን ሀይከል፡፡

በኒዮሊበራሊዝም ላይ…

ድንበር ተሻጋሪ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች (Multinational Corporations) በኢኮኖሚ የበላይነትን መያዛቸው በዴሞክራሲያዊ አግባብ የተመረጡ ነገር ግን የእነርሱን ዓላማና ፍላጎት የማይቀበሉና የማያስፈጽሙ መንግስታትን እንዲገለበጡ ያደርጋሉ የሚል ተደጋጋሚ ወቀሳ ይሰማል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ኩባንያዎች በአንድ ሀገር ያላቸውን ካፒታል (ሀብት) ባልተጠበቀ ጊዜና ሁኔታ ጠራርገው ቢወጡ የሀገራቱን ኢኮኖሚ እንዳልነበር አድርጎ ስለሚያሽመደምደው ታዳጊ ሀገራትን የእነርሱ ባሪያ ያደርጋቸዋል የሚል ስጋትም ይደመጣል፡፡

የኒዮሊበራል አስተሳሰብ ደጋፊዎች በበኩላቸው ድንበር ተሻጋሪ ኮርፖሬሽኖች በታዳጊ ሀገሮች የሚያፈሱት ገንዘብ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በ 1970 ዎቹ የነበረውን ሁኔታ በምሳሌነት በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ እነሱ እንደሚሉት ነፃ ገበያን በ 1970 ዎቹ የነበረው የኢኮኖሚ አለመረጋጋትና ቀውስ ዓይነት ሁኔታዎች ይበልጥ እንዳይበገር በማድረግ የተሻለ እድገት ለማስመዝገብና ልማትን ለማምጣት ይረዳል ይላሉ፡፡ በሁሉም ሀገሮች እንዲህ ዓይነት የእድገት ሁኔታ መኖሩ ዓለም አቀፍ መረጋጋትን ብሎም ዴሞክራሲያዊ መንግስታትን ለመመስረት ይረዳል ይላሉ፡፡

ሀር በርክሌይ እና ፕሮፌሰር ብራድ ዲሎንግ እንደሚሉት ከሆነ፣ “ኒዮሊበራል” (Neoliberal) በሚለው ላይ የተጨመረው “ኢዝም” (ism) የሚል ቅጥያ ሁለት ነገሮችን ያመለክታል፡፡ “አንደኛ፡- በኢንዱስትሪ የበለጸጉ እና በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች በኢኮኖሚው መስክ መቀራረባቸው ለቴክኖሎጂ ሽግግር እና ለእድገት አስፈላጊ በመሆኑ በዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ላይ እንቅፋት የሆኑ መሰናክሎች መወገዳቸው አስፈላጊ ነው፡፡ ሁለተኛ፡- መንግስታት በአጠቃላይ ታላላቅ የኢንዱስትሪና የንግድ ተቋማትን ለመምራት አቅም ያንሳቸዋል፡፡ እናም፤ ከመሰረተ-ልማት፣ ከአስተዳደር ፍትህና ፀጥታ ተቋማት ውጪ ያሉ በመንግስት ይዞታ ስር ያሉ ተቋማት ሁሉ በሽያጭ ወደ ግል ይዞታ መዞር ይኖርባቸዋል የሚል መንፈስን የሚያስተጋባ ነው” ይላሉ፡፡

የኒዮሊበራል አስተሳሰብን የሚተቹ ወገኖች በበኩላቸው “እነዚህ ሁለት የኒዮሊበራሊዝም መርሆዎች የ‘ማንጠብጠብ ንድፈ ሃሳብ’ (Trickle down Theory) ማሳያዎች ናቸው፡፡ ይህም ማለት በነፃ ገበያ የካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ ‘የሀብት ባለቤትነት በዋናነት በበለፀጉት ሀገሮች ከበርቴዎች መዳፍ ስር ቢሆንም የኢኮኖሚ እድገትና የቴክኖሎጂ ሽግግር፤ ድሃ ሀገሮችንና ድሃ ሕዝባቸውን ተጠቃሚ ያደርጋል’ የሚል አስተሳሰባቸውን ያሳያል” በማለት ይተነትኑና “ይሁን እንጂ፣ ሀብታሞችን የበለጠ ሀብታም ከማድረግ ውጪ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ እንደሚባለው ለድሃው ጠብ የሚል ነገር የለም፡፡ ይባስ ብሎ ድሃው በድጎማ መልክ የሚያገኘውን ጥቅም እያጣ ነው፣ ከስራ እየተፈናቀለ ነው…” የሚል አስተያየት ያቀርባሉ፡፡

የኒዮሊበራሊዝም አስተሳሰብ አቀንቃኞች በበኩላቸው “እድገት በራሱ ነፃነት ነው፡፡ የላቀ እድገትና ስፔሽያላይዜሽን ግለሰቦችን የበለጠ ተጠቃሚ ያደርጋሉ፡፡ መንግሥት በኢኮኖሚው መስክ ጣልቃ እንዲገባ የሚፈቀድ ከሆነ ግን መንግስት አንዳንድ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ በሚወስደው ብድር ምክንያት ለትውልድ የሚተርፍ እዳ ከመቆለል የዘለለ ለድሃው የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም፡፡ በዘመነ ግሎባላይዜሽን የታሪፍ ከለላ እና የኢኮኖሚ ጥበቃ በማድረግ ድንበርን መከርቸምም የሚያዋጣ አደለም” ይላሉ፡፡

ኒዮሊበራሊስቶች ዓለም አቀፍ ዜግነት እየተፈጠረ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ለዚህም ሲባል “ዓለም አቀፍ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርዓትን በሀገሮች መካከል በሚደረግ ድርድርና ስምምነት መፍጠር ይቻላል” ይላሉ እነዚሁ ኒዮሊበራሊስቶች፡፡ አክለውም “ከፍ ያለ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መደጋገፍ የላቀ እድገት ያስገኛል፣ በሀገሮች መካከል ጦርነት እንዳይነሳ ያደርጋል፣ ችግርን በውይይትና በድርድር ለመፍታት ይረዳል…” ይላሉ፡፡

ራሳቸውን “የሊበርታሪያን” (ከኒዮሊበራሊዝም በኋላ እያቆጠቆጠ ያለ አስተሳሰብ ነው) አስተሳሰብ እናራምዳለን የሚሉ ሌሎች ወገኖች በበኩላቸው ይህ የኒዮሊበራሎች አስተሳሰብ የግለሰቦችን የመወሰን መብትና ነፃነት የሚሸረሽር ነው በማለት ይቃወሙታል፡፡

የኒዮሊበራሊዝም አልፋና ኦሜጋ “ነፃነት” የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ይኸውም፤ የግለሰብ ነፃነት፣ የኢኮኖሚ ነፃነት፣ ሀብት የማፍራት ነፃነት፣… እየተባለ የሚገለጸው ማለት ነው፡፡ እውነት ግን ይህ ነፃነት ኒዮሊበራስቶቹ አልመው ባስቀመጡት መሰረት እውን ሊሆን ችሏል? ዳንኤል ብሩክ (2007)፣ ሮበርት ፍራንክ (2007)፣ ሮበርት ቸርኖማስና ኢያን ሐድሰን (2007) የተባሉ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ባደረጉት ጥናት ይህ የኒዮሊበራስቶች ዓላማ እውን ሊሆን አለመቻሉን አረጋግጠናል ይላሉ፡፡ “ገበያውም ነፃ አልሆነም፣ ግለሰቦችም ነፃ አልሆኑም” ይላሉ ምሁራኑ፡፡

የኒዮሊበራሊዝም የፖለቲካ ኃይሎች የሚከተሉት የገበያ አክራሪነት መርህ የህብረተሰብን ማህበራዊ ደህንነት ማረጋገጥ ቀርቶ “ማህበራዊ ዳርዊኒዝምን” (social darwinism) እየፈጠረ እንደሆነ ምሁራን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በመናገር ላይ ናቸው፡፡ “ከ 37 ጎልማሳ አሜሪካውያን አንዱ እስር ቤት ነው… የማህበራዊ ዋስትና በጀት እንዲቀነስ በመደረጉ ግጭት በዝቷል፡፡ እናም፤ በኒዮሊበራል የአስተዳደር ዘመን የእስር ቤት ግንባታው በላቀ ደረጃ ተከናውኗል፡፡ በካሊፎርኒያ ብቻ በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የሌለው የእስር ቤት ግንባታ ፕሮግራም ተካሂዷል” ይላሉ፡፡ አንጄላ ዴቪስ የተባሉ ምሁር በበኩላቸው “ክሊንተን የተከተሉት የኒዮሊበራል ፖሊሲ ለአሜሪካ ብዙሃን ህብረተሰብ ዘመናዊ ባርነትን ያሰፈነ፣ እስር ቤትን ያስፋፋ የኢኮኖሚ እድገት ነበር” ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ፤ ከላይ የተጠቀሱት አስተያየቶች ሲታዩ ኒዮሊበራሊዝም አብዮታዊ ሊበራል ለውጥ (Revolutionary Liberal Change) የሚያስፈልገው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ምን ተደረገ?

ድሃ (ታዳጊ) ሀገሮች የኒዮሊበራሊዝምን መርሆዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ በማድረግ የዓለም አቀፍ ኮርፖሬሽኖችን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ዓለም

ባንክ እና ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ዋነኞቹ መሳሪያዎች ሲሆኑ፣ እንደ አሜሪካና እንግሊዝ ያሉ የበለጸጉ ሀገራትም ተጽእኖ የመፍጠር አቅማቸውን ለዚሁ ተግባር ይጠቀሙበታል፡፡

አንዳንድ ወገኖች ዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ታዳጊና ድሃ ሀገሮች ልማትን እንዲያሳልጡ ይረዳሉ ሲሉ፣ ሌሎች ወገኖች ደግሞ የለም እነዚህ የብሪተን ውድስ ተቋማት (Breton Woods) (ብሪተን ውድስ አሜሪካን ሀገር በኒው ሐምፕሻየር ግዛት ውስጥ 43 ሀገራት እነዚህን ተቋማት ለመመስረት የተፈራረሙበት ስፍራ ነው) የበለፀጉ ሀገሮች ሜጋ ኩባንያዎች ጥቅም አስጠባቂዎች ናቸው ይላሉ፡፡

ዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ዴሞክራሲያዊ አሰራርም ሆነ መርህ የሌላቸው ተቋማት ናቸው፡፡ በእነዚህ ተቋማት ውሳኔ የሚተላለፈው እያንዳንዱ ሀገር በሚያዋጣው ዓመታዊ የመዋጮ መጠን እንዲሆን መደንገጉ፤ ከበርቴ ሀገሮች በታዳጊ ሀገሮች ላይ የሚፈልጉትን ውሳኔ ለማሳለፍ እንዲችሉ ታልሞ የተቀየሰ ዘዴ ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ የአሜሪካንን ሁኔታ ብቻ ማየት በቂ ነው፡፡ አሜሪካ በእነዚህ ተቋማት ያላት የመወሰን ድርሻ አስራ ሰባት በመቶ (17%) ነው፡፡ በሁለቱ ተቋማት ውሳኔ የሚተላለፈው ደግሞ ሰማንያ አምስት በመቶ (85%) ድርሻ ባላቸው ሀገሮች ድጋፍ ሲያገኝ ነው የሚል አሰራር በመኖሩ፤ በአንድ ጉዳይ ላይ ሁሉም አገሮች ተስማምተው አሜሪካ ብቻዋን አልስማማም ብትል ውሳኔው ውድቅ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህም አሜሪካ ድምፅን በድምፅ የመሻር መብት (Veto Power) ያላት መሆኑን ያመለክታል፡፡

የዓለም የንግድ ድርጅትን (WTO) ሁኔታ ያየን እንደሆነ አንድ ሀገር ያለው የገበያ መጠን የመደራደር አቅሙን የሚወስነው በመሆኑ፤ የከበርቴ ሀገሮች የበላይነት የተረጋገጠ ነው፡፡ ድሃ ሀገሮች ስምምነት የተደረሰባቸውን የንግድ ህጎች አናከብርም ቢሉ ያደጉት ሀገሮች ማዕቀብ በመጣል ኢኮኖሚያቸውን ሊያሽመደምዱት ይችላሉ፡፡ እናም፤ የኒዮሊበራል መርሆዎች አስፈጻሚ የሆነው የዓለም የንግድ ድርጅት በድሃና በሀብታም ሀገሮች መካከል ሊኖር የሚገባውን እኩልነት የሚያረጋግጥ ሳይሆን የጌታና የሎሌ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡ በዓለም የንግድ ድርጅት በኩል የሚደረጉ ስምምነቶች የተራዘመ የታክስ እፎይታንና ከቀረጥ ነፃ መብትን ላደጉት ሀገሮች ባለሀብቶች በመፍቀድ ያደጉት ሀገሮች ባለሀብቶችን የበለጠ ተጠቃሚ የሚያደርግ አድሎአዊ ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑ ይስተዋላል፡፡

በአጠቃላይ፤ የኒዮሊበራሊዝም የነፃ ገበያ መርሆዎች ስራ ላይ እንዲውሉ የሚፈለገው በታዳጊ ሀገሮች ላይ እንጂ በበለፀጉት ሀገሮች ላይ አለመሆኑ ይታያል፡፡ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ቢኖሩም ክንደ ፈርጣማዎቹ አሜሪካና እንግሊዝ ከስምምነቶቹ ውጪ ለየሀገሮቻቸው ባለሀብቶች የታሪፍና የፓተንት ከለላ፣ ለገበሬዎቻቸው ድጎማ ማድረጋቸው ይነገራል፡፡ እ.ኤ.አ በ 2008 ለተከሰተው የፋይናንስ ቀውስ ማካካሻ ለባንኮች የተደረገው ክፍያም (Bailout) የሚያሳየው ይህንኑ ነው፡፡ ለዚህም ነው አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች “ኒዮሊበራሊዝም ማለት ለሀብታሞች የመንግስት ጣልቃ ገብነትን፣ ለድሃዎች ነፃ ገበያን የሚፈቅድ መርህ ነው” የሚሉት፡፡

የኒዮሊበራሊዝም ጰጳሳቱ የራሳቸውን ሀገር ከሸቀጣ ሸቀጥ ማራገፊያነት በመከላከልና ከለላ በማድረግ የኒዮሊበራሊዝም መርሆዎችን እየናዱ፣ አቅምየለሽ ታዳጊ ሀገሮች ሕጎቹን በጥብቅ እንዲያከብሩ ጥዋት ማታ መወትወታቸው የኒዮሊበራሊዝምን ይሉኝታቢስነት ብቻ ሳይሆን አስተዛዛቢነቱንም የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ በአጠቃላይ፤ እ.ኤ.አ በ 2008 ከተከሰተው የፋይናንስ ቀውስ በኋላ በኒዮሊበራሊዝም ላይ መጠነ ሰፊ ተቃውሞ ተነስቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ኒዮሊበራሊስቶቹ የምዕራብ ሀገራት መንግስታት በኢኮኖሚው ወስጥ እጃቸውን እስከ ክንዳቸው ነክረው የቀውስ ማካካሻ (Bailout)፣ የእዳ ማካካሻ፣ በጀት ቅነሳ፣… የሚሉ መፍትሄዎችን ተግባራዊ ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ ይህም “ኒዮሊበራሊዝም እንዲፈጠር ምክንያት የሆነን ቀውስ የኒዮሊበራሊዝምን መርሆዎች በመጣስ የመመከት ተግባር ነው” ይላሉ አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች፡፡ ነገሩ ግን እንደ አሜሪካ ባሉ ሀገሮች ጭምር ዎል ጎዳናን እንውረር (Occupy Wall Street) የሚል ማህበራዊ እንቅስቃሴ መፍጠሩን አሳይቷል፡፡

*መደምደሚያ*

ኒዮሊበራሊስቶች በአጠቃላይ የሚያቀነቅኑት የዋጋ ቁጥጥር፣ አላስፈላጊ ድጎማ፣ የውጪ ምንዛሬ ትመና፣ ተደራራቢ ቀረጥ፣ በገቢ ላይ እየጨመረ የሚሄድ ታክስ፣ የጉልበት ዋጋ ትመና፣ ጊዜና ጉልበት የሚጨርስ ቢሮክራሲያዊ አሰራርንና የመሳሰሉትን ነው፡፡ እነዚህን “ገበያው ይወስናቸው” ነው የሚሉት ሊበራሊስቶች፡፡ እውነቱን ለመናገር እነዚህን ነገሮች በምድር ላይ ማንም ሰው ሊወዳቸው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ማንም ሰው የተወሳሰበ ቢሮክራሲን አይወድም፣ ገቢው የሚቀንስበትን ተደራራቢ ታክስ አይወድም፣… ወዘተ. ስለሆነም፣ ሊበራሊስቶች አሉትም አላሉት በየትኛውም የኢኮኖሚ ስርዓት እነዚህ ነገሮች ሊወደዱ አይችሉም፡፡ ሊወገዱም ይገባል፡፡

ኒዮሊበራሊዝም ከሚያቀነቅናቸውና ተግባራዊ እንዲደረጉ ከሚፈልጋቸው የኢኮኖሚ መርሆዎች አንዱ “Deregulation” የሚል ነው፡፡ ይህ ማለት “ምንም ዓይነት ህግ አይኑር ማለት አደለም” ይላሉ ኒዮሊበራሊስቶች ራሳቸው፡፡ ኒዮሊበራሉዝም እንዲያውም የገበያ ተቋማትን የሚመራና ስራቸውን የሚያሳልጥ ህግ እንዲኖር ይፈልጋል ይላሉ፡፡ “እኛ የማንፈልገው ለዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ መሰናክል የሚሆኑ ህጎችን ነው፡፡ እነዚህ ይወገዱ እንላለን” ይላሉ፡፡ እንዲያውም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፤ “Liberalization” የሚለውን ሀሳባቸውን “ሊያሰራ የሚችል የገበያ ሁኔታ” ይፈጠር (Market Enabling) ወደማለት ተሸጋግረዋል፡፡ “Deregulation” ሳይሆን Re-regulation ወደማለት ተረማምደዋል፡፡ ይሄ ደግሞ በ 1990 ዎቹ ተጀምሮ የነበረው የመዋቅር ማስተካከያ ቀጣይ ክፍል ይመስላል፡፡

በርግጥ ባለፉት 40 ዓመታት ገደማ “Deregulation፣ Liberalization፣ Privatization” የሚሉት የኒዮሊበራሊስቶች መርሆዎች በበርካታዎቹ

የዓለም ሀገራት ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ዋነኛ ዓላማውም ኢኮኖሚን ለማሳደግ፣ ድህነትን ለማስወገድ ነው ሲባል ነበር፡፡ ውጤቱ ሲታይ ግን ኢኮኖሚውም አላደገም፣ ድህነቱም ከነበረበት ፈቀቅ አላለም፡፡ ይባስ ብሎ ማህበራዊ ቀውሱ ተባብሷል፡፡ ስራአጥነቱ ከፍቷል፡፡ የኒዮሊበራሊዝም የኢኮኖሚ መርሆዎች ትርፍ እንዲጨምር እንጂ ፍትሃዊ የገቢ መጠን እንዲፈጠር የማያደርግ በመሆኑ በድሃውና በሜጋ ከበርቴው መካከል ያለውን ልዩነት ያሰፋል፣ ይህም ዴሞክራሲን ያጠፋል ሲሉ ራሳቸው የኒዮሊበራሊዝም ርእዮት አራማጆች ስጋታቸውን ይገልጻሉ፡፡

በዚህም ምክንያት እንደ ሚልተን ፍሬድማን የመሳሰሉ ታዋቂ ኢኮኖሚስቶች “ሽጡ!” (Privatize) የሚል አባዜአቸውን ቆም ብለው ወደ መፈተሽና አማራጭ ሀሳቦችን ወደ ማውጠንጠን የተሸጋገሩ ይመስላል፡፡ እናም “ሽጡ!” (Privatize) ከሚለው ሌላ መናጆ ሆነው የሚተገበሩ ሙስናን አስወግዱ፣ ሰብአዊ መብት አክብሩ፣ ማህበራዊ ዋስትና አድርጉ፣ ድህነት ቅነሳ፣ ኮርፖሬት ሲትዝንሽፕ፣… የሚሉ ቅመሞች እንዲጨማመሩ ሃሳብ እየሰነዘሩ ነው፡፡ በአጠቃላይ፣ የኒዮሊበራሊዝምን ታሪካዊ አመጣጥና የተግባር እርምጃዎች ስናጤን የምንገነዘበው ነገር ይህ የኢኮኖሚ መርህ ሆን ተብሎ ስራ ላይ እንዲውል የተደረገበት ዋነኛ ምክንያት፤ የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመጥቀም መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም፣ ይህ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ጥቂት ሰዎችን ለመጥቀም አቅደው የዘረጉትን አሰራር ተጠቃሚ ያልሆኑት ብዙሃን፤ ሂደቱ አሁን ያለበት ቦታ ላይ እንዲቆም በማድረግ በቀጣይ ሁሉንም የሚጠቅም አማራጭ መፈለግ አለበት የሚል አስተያየት በስፋት ይደመጣል፡፡ (ስለ ልማታዊ መንግስት ይቀጥላል)